ERICSSON

# የእጅ አያያዝ

## Standard

2021-06-22

## ይዘቶች


1 **መግቢያ** ... 3

2 **መስፈርቶች** ... 3

3 **የግል መከላከያ እቃ** ... 4

4 **የህክምና ብቁነት እና ምላሽ** ... 4

5 **የስጋት ግምገማ እና እቅድ አወጣጥ** ... 4

5.1 መሸከም ... 4

5.2 ቁጥጥር ... 5

6 **ስልጠና** ... 6

7 **ቁጥጥር እና ግምገማ** ... 6

8 **የለውጥ መረጃ** ... 6



© Ericsson AB 2021

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ የኤሪክሰን ንብረት ነው። በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ ያለምንም ማሳወቂያ ይለወጣል እናም ለእውነታዎች ትክክል አለመሆን እና ለህትመት ስህተቶች ኤሪክሰን ሀላፊነቱን አይወስድም።

# 1 መግቢያ

እንደዚህ አይነት ስራ የሚሰሩ ግለሰቦች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ጤና እና ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ ይህ ደንብ የእቃዎችን የእጅ አያያዝ አነስተኛ መስፈርቶች ይገልጻል።

መስፈርቶቹ የእቃዎችን በእጅ መያዝን (ምሳሌ፡ ማንሳት፣ ማውረድ፣ መግፋት፣ መሳብ፣ መሸከም፣ መያዝ) ለሚያካትቱ ለሁሉም ተገቢ የስራ ተግባራት በስራ ላይ ይውላሉ። ኬሚካሎችን መያዝ በዚህ ደንብ ስጥ አልተካተተም፤ ነገር ግን በኬሚካል አያያዝ ደንብ ተገልጿል።

በዚህ ደንብ ውስጥ የአካባቢው ህግ መስፈርቶቹን በሚበልጥበት ጊዜ የአካባቢው ህጋዊ መስፈርቶች ተግባራዊ ይሆናሉ።

# 2 መስፈርቶች

በእጅ የሚሰሩ ስራዎችን በሚሰሩበት ጊዜ የሚከተሉትን መስፈርቶች መከተል አለብዎት:

- በእጅ የሚሰሩ ተግባራት ሰራተኞችን ወይም ሌሎችን ተቀባይነት የሌለው ስጋት ላይ ማስቀመጥ የለባቸውም፣
- ነፍሰ ጡር የሆኑ ወይም ከዚህ ቀደም የነበረ የጡንቻ እና የአጥንት ህመም ያለባቸው ሰራተኞች በእጅ የሚሰሩ ተግባራትን መስራት የለባቸውም፣
- በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ ፍቃድ ባለው ወይም ለመጠቀም በሰለጠነ ግለሰብ የማሽን መስሪያ እቃ ጥቅም ላይ ይውላል።
- በእጅ የሚሰሩ ስራዎችን ማጥፋት ካልተቻለ፣ መወገድ የማይችልን የማንኛውም በእጅ የሚሰራ ስራን የአደጋ ስጋት ይገምግሙ እና በእጅ ስራ የሚመጣ አደጋን ይቀንሱ፤ እስካሁን ተግባራዊ የሆነ ነው፣
- የቁጥጥር እርምጃዎች ወይም መፍትሄ ውጤታማነትን ይገምግሙ፣
- አሰፈላጊ ተግባራትሌሎችን አደጋ ላይ እንዳይጥሉ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፣
- አንድ ሰው ብቻውን ከባድ እቃዎችን ለማንሳት መሞከር የለበትም፣
- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ያሉ ሰዎች ሸክም በሚያነሱበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ ሰው እኩል ማንሳቱን ለማረጋገጥ ከቡድኑ አንድ ሰው ይመረጣል እና ቡድኑ አንድ ላይ ይሰራል፣
- በሰራተኞች የሚለበሱ ልብሶች፣ ጫማ ወዘተ ደህንነቱ የተጠበቀ የእጅ ስራን መከልከል የለባቸውም፣ ለምሳሌ የሚንሸራተቱ ጓንቶችን፣ ቀላል ጫማ እና በሚሸከሙበት ጊዜ የሚያስቸግሩ ሰፊ ልብሶችን ያስወግዱ። ልብሱ በጣም የሚያጣብቅ ሆኖ እንቅስቃሴ አለመገደቡን ያረጋግጡ፤ እና
- ሸክሞችን በጉልበቱ እንዲሰራ የሚጠበቅበት ሰው ተገቢ የእጅ አሰራር ስልጠና ይቀበላል

# 3 የግል መከላከያ እቃ

ለስራው ተገቢ የሆነ የመከላከያ እቃ መለበስ አለበት:

- እጅን የመቁረጥ ስጋት ሲኖር ተገቢ ጥራት ያላቸው ጓንቶች(ምሳሌ፡ ቅልጥፍናን እና የመቆረጥ መከላከልን ከግምት ውስጥ በማስገባት)፣
- የሚከላከል ጫማ፣ እና
- ደህንነቱ የተጠበቀ የእጅ ስራን የማይከለክል ተገቢ ልብስ (ምሳሌ፡ በሚሸከሙበት ጊዜ ሊያስቸግር ስለሚችል ሰፊ ልብስ ሊወገድ ይገባል)።

# 4 የህክምና ብቁነት እና ምላሽ

በህግ ሲፈቀድ የሰራተኛው የጤና ሁኔታ የአካባቢው የስጋት ግምገማ አካል ሊሆን ይገባል።

# 5 የስጋት ግምገማ እና እቅድ አወጣጥ

የእጅ ስራ ተግባር መወገድ በማይችልበት ጊዜ ለስጋቶች ሊገመገም ይገባል። እቃ ማንሳት የእጅ ስራ አንድ መንገድ ሲሆን አደጋዎች እንዲመጡ በብዛት የሚያደርግ እና በዚህ መመሪያ ላይ የስጋት ግምገማ ውስጥ እንዴት ከግም ውስጥ እንደምናስገባ እንደ ምሳሌ ጥቅም ላይ ይውላል።

## 5.1 መሸከም

በእጅ የሚሰራ ስራ መሸከምን በሚያካትትበት ጊዜ፣ የስጋት ግምገማው አራት መንስኤዎችን ሊያካትት ይገባል: ስራ፣ ሸክም፣ የስራ አካባቢ እና የግለሰብ አቅሞች ናቸው።

**ስራ**፣ ሸክም ላይ በሚሰሩበት ጊዜ ከሰራተኞች የሚጠበቁ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያተኩር፣ ከታች ባሉት አመለካከቶች ሊገመገም ይችላል:

- ሸክሙ የሚነሳበት፣ የሚወሰድበት፣ ወይም የሚቀመጥበት ከፍታ፣
- የስራው ድግግሞሽ፣
- የስራ-ተመን፣
- የሚሸከምበት ርቀት፣
- የተፈቀዱ የእረፍት ሰአቶች፣ እና
- የማይመች አቋቋም፣ ማጎንበስ (እግሮችን ቀጥ አድርጎ ጀርባን ማጠፍ)፣ መጣመም (እግር ባለበት ቦታ ሆኖ ትከሻን ማዞር)፣ ወደ ቋሚ ርቀት ሸክምን ማንሳት፣ ከትከሻ ከፍታ በላይ መድረስ፣ ሸክሙን ከሰውነት አርቆ መያዝ እና የመሳሰሉትን ይመስላል።

**ሸክም**፣ ስራ የሚሰራበት ሸክም ላይ የሚያተኩር፣ ከታች ባሉት አመለካከቶች ሊገመገም ይችላል:

- ክብደት፣
- መጠን፣

- ቅርጽ እና ጠርዝ፣
- ለመያዝ አመቺነት፣
- የስበት ማእከል፣
- የመያዣ(ዎች) መኖር፣
- ሙቀት፣ እና
- ሌሎች ለአደጋ የሚያጋልጡ

**የስራ አካባቢ፣** ስራው የሚሰራበት አካባቢ ላይ የሚያተኩር፣ ከታች ባሉት አመለካከቶች ሊገመገም ይችላል:

- ባለው የስራ ቦታ ላይ እገዳዎች፣
- የወለል ገጽ እና የወለል ደረጃዎች ላይ ለውጦች፣
- የብርሐን ደረጃ፣ እና
- ሙቀት እና እርጥበት።

**የግለሰብ ችሎታዎች፣** የሚሰራውን ተግባር የሚያከናውነው ሰራተኛ ጋር የሚያተኩረው፣ ከታች ባሉት አመለካከቶች ሊገመገም ይችላል:

- ከሰራተኞች የሚጠበቅ ያልተለመደ ችሎታ (ለምሳሌ ያልተለመደ ጥንካሬ፣ብርታት፣ መጠን ወይም ቴክኒክ)፣ እና
- ለተጋላጭ ግለሰቦች ከፍተኛ ስጋት፣ ለምሳሌ ነፍሰጡር ሴቶች ወይም ከዚህ በፊት የጀርባ፣ የጅማቶች ወይም የጡንቻ አደጋዎች ያለባቸው ሰራተኞች።

## 5.2 ቁጥጥር

በእጅ የሚሰሩ ስራዎች አደጋ ቁጥጥር ከታች ያሉትን የቁጥጥሮች ቅደም ተከተል በመጠቀም ሊከወን ይችላል:

- በእጅ የሚሰራውን ተግባር በአውቶማቲክ ወይም በማሽን በመጠቀም የእጅ ስራን ማስወገድ፣

- የእጅ ስራን የማያስወግዱ ነገር ግን ቀላል የሚያደርጉ ለመያዝ የሚረዱ ነገሮችን መጠቀም፣

- ስራውን በሚከተሉት ማሻሻል:
  - አንድ ሰራተኛ ግለሰብ ስራውን ማከናወን ያለበትን የጊዜ ርዝመት ለመቀነስ የእረፍት ሰአት ወይም የስራ ማቀያየርን በማስጀመር ተደጋጋሚ የእጅ ስራን መቆጣጠር፣
  - የስራ ጣቢያውን አዘገጃጀት በመቀየር ማጎንበስ፣ መጣመም እና የመሰሳሉትን የማይመቹ አቋቋሞች ማስወገድ፣ እና
  - ከወለል ላይ ማንሳትን ለማስወገድ ሸክሙን ወደ ወገብ ከፍታ ለማምጣት ጠረጴዛ ወይም ሊፍት መጠቀም

- ሸክምን በሚከተለው ማሻሻል:
  - ከባድ ሸክምን ወደ ትንንሽ ክፍሎች መሰባበር፣
  - ትልቅ፣ ብዙ ሸክም ላይ ለመስራት ከአንድ ሰው ይልቅ ብዙ ሰራተኞችን መጠቀም፣

- የሚንቀሳቀስ ሸክምን በደንብ በመያዝ ወይም ማስቀመጫ ውስጥ በማድረግ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ፣
  - የመሬት ስበት ማእከሉ የት እንዳለ ማየት እንዲቻሉ የመሬት ስበት ማእከሉ መካከለኛ ያልሆነበት ሸክም ላይ ምልክት ማድረግ፣ እና
  - ለመያዝ አስቸጋሪ የሆነ ሸክም ላይ የእጅ መያዛ ማስገባት።

- አካባቢውን በሚከተለው ማሻሻል
  - የእጅ ስራን ተግባር ለመስራት ሰፊ ክፍተት እንዲኖር የስራ ቦታውን እንደገና ማዘጋጀት፣
  - ለማንቀሳቀስ እና ለመደራረብ የተዛባ ወለልን ማስተካከል፣ እና
  - በደንብ ብርሃን የሌለበት ቦታ ላይ ተጨማሪ ብርሀን ማቅረብ።
- ስራው እና የግለሰብ አቅሞች መመጣጠናቸውን ማረጋገጥ። ለምሳሌ፣ ተግባሩ ያልተለመደ ችሎታ የሚጠይቅ ከሆነ፣ ሰራተኛው ይህ ችሎታ ሊኖረው ይገባል፤ ቴክኒክ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ቴክኒኩ እንዲኖራቸው ሰራተኞቹ መሰልጠን አለባቸው።

## 6 ስልጠና

የእጅ ስራ አሰራር ስልጠና ለሰራተኞች ስጋቶችን የማወቅ እና ስራዎችን የማከናወኛ ምርጥ መንገዶች ላይ የመወሰን ችሎታ ይሰጣቸዋል።

## 7 ቁጥጥር እና ግምገማ

ከዚህ ደንብ ጋር መስማማት የሚከተሉትን በመገምገም እና መዝገቦች በማስቀመጥ ቁጥጥር ይደረግበታል:

- የአጋጣሚዎች ስታትስቲክስ፣
- የኢንሹራንስ ይግባኝ ሪፖርቶች፣
- ስልጠና፣ እና
- የቁጥጥር እርምጃዎች ወይም መፍትሄዎች ውጤታማነት ግምገማ።

## 8 የለውጥ መረጃ

ከመጨረሻው ግምገማ ጀምሮ የነበሩ ለውጦች:

1 መግቢያው እንደገና ተጽፏል

2 መስፈርቶች እንደገና ተጽፈዋል እና ይዘት ተጨምሯል

3 የህክምና ብቁነት እና ምላሽ ተጨምሯል

4 የስጋት ግምገማ እና እቅድ አወጣጥ እንደገና ተጽፏል እና ይዘት ተጨምሯል